**የኤሌክትሪክ ደህንነት**

ማብሪያና ማጥፊያን መጠቀም ፣ የቡና ማፍያን ሶኬት መሰካት፣ ላፕቶፕ ኮምፒውተርን ቻርጅ ማድረግ ፡-እነዚህ ብዙዎቻችን በቀላሉ የምናደርጋቸው ነገሮች ናቸው። ኤሌክትሪክ ህይወታችንን ቀላል ያደርገዋል። ይሁን እንጂ ጥንቃቄ ማድረግ እና ደህንነትን ሁል ጊዜ ማስታወስ ይኖርብናል።

**የደህንነት ምክሮች**

- ሁሉንም የኤሌትሪክ ስራዎች ብቃት ባለው ኤሌክትሪክ ባለሙያ ያሰሩ።
- ቤት ሲገዙ ወይም ሲያድሱ ብቃት ባለው የኤሌትሪክ ባለሙያ እንዲታይ/ እንዲፈተሽ ያድርጉ።
- ሙቀትን የሚለቁ መገልገያዎችን (እንደ ቡና ማፍያ ፣ ቶስተር፣ ማሞቂያ፣ ወዘተ) በአንድ ጊዜ አንዱን መገልገያ ብቻ ሶኬት ላይ ይሰኩ።
- ዋና ዋና መገልገያዎች (ማቀዝቀዣዎች ፣ የልብስ ማድረቂያዎች ፣ የልብስ ማጠቢያዎች ፣ ማብሰያዎች ፣ አየር ማቀዝቀዣዎች ፣ ወዘተ) በቀጥታ ግድግዳ ላይ ባሉ የኤሌትሪክ ሶኬቶች ላይ መሰካት አለባቸው። የኤሌክትሪክ ገመዶች እና የኤሌክትሪክ መሰኪያ ገመዶችን መጠቀም የለብዎትም።
- አርክ ፎልት ሰርኪውት ኢንተራፕተርስ (AFCIs) አደገኛ ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ ኤሌክትሪክን የሚያቋርጥ የሚዘጋ (circuit break)ነው። በቤትዎ ውስጥ እንዲገጠሙ ያድርጉ። ብቃት ያለው ኤሌትሪክ ባለሙያ ይጠቀሙ።
- የኤሊክትሪክ አደጋን ለመቀነስ ግራውንድ ፎልት ሰርኪውት ኢንተራፕተርስ (GFCI) ይጠቀሙ። ጂኤፍሲአይ (GFCI) አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያን ይዘጋል። በቤት ውስጥ ባሉ የተለያዩ ክፍሎች ማለትም በመታጠቢያ ቤት፣ በማብሰያ ክፍል፣ በጋራዦች እና በቤዝመንት ውስጥ መገጠም አለባቸው። ሁሉም ከቤት ውጪ ያሉ የኤሌክትሪክ ሶኬቶች ጂኤፍሲአይ (GFCI) ያላቸው መሆን አለባቸው።
- ኤኤፍሲአይ (AFCI) እና ጂኤፍሲአይ (GFCI) በትክክል እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በወር አንድ ጊዜ ይፈትሹ።
- የኤሌክትሪክ ገመዶች በበሮች ወይም በምንጣፎች ስር እንደልተዘረጉ እርግጠኛ ይሁኑ። የኤክስቴንሽን ገመዶች ለጊዜያዊ አገልግሎት እንዲውሉ የታሰቡ ናቸው። የኤክስቴንሽን ገመዶችን ላለመጠቀም፣ ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ሶኬቶች ብቃት ያለው የኤሌትሪክ ባለሙያ እንዲገጥምልዎት ያድርጉ።
- ከሚመከረው የኤሌክትሪክ መጠን ጋር የሚዛመዱ አምፖሎችን ይጠቀሙ። የሚመከረውን የኤሌክትሪክ መጠን (wattage) የሚገልጽ የተለጠፈ መግለጫ መኖር አለበት ።

አስፈላጊ ማስታወሻዎች

የሚከተሉት ከተከሰቱ ብቃት ላለው የኤሌትሪክ ባለሙያ ወይም ለአከራይዎ ይደውሉ፡-

- ፊውዝ አዘውትሮ የሚፈነዳ ከሆነ ወይም ብሬከር ቶሎ ቶሎ የሚዘጋ ከሆነ።
- የኤሌክትሪክ መገልገያ ዕቃዎችን ሲነኩ የሚነዝር ስሜት የሚሰማዎት ከሆነ።
- ከለራቸው የተቀየረ ወይም የሚሞቁ የግድግዳ ሶኬቶች ።
- ከመገልገያ እቃዎች የሚወጣ የተቃጠለ ወይም የጎማ ሽታ።
- ብልጭ ድርግም የሚሉ ወይም የደበዘዙ መብራቶች።
- ከሶኬቶች የሚወጡ ብልጭታዎች ።

<u>ለነጻ</u> የቤት ደህንነት ፍተሻ ወደ 311 ይደውሉ